# ክፍለ ጊዜ 4 የ5ኛ ክፍል ውጤት የወላጆች መመሪያ

በማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ 4፣ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለፁት ፅንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።
እባክዎ ልብ ይበሉ፦ በ በኢታሊክስ የታዩት ጽንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ትምህርት ተሰጥቶባቸዋል ነገር ግን በሪፖርት ካርዱ ላይ ዉጤት አልተገለጸም።

## ሒሳብ

### መለካት እና የተመዘገበ መረጃ

- በአንድ በተሰጠ የልኬት ስርዓት ውስጥ በመጠን በተለያዩ መደበኛ መስፈርት መለኪያዎች/ዩኒቶች መለወጥ (ለምሳሌ፦ 5 ሴንቲሜትርን ወደ 0.05 ሜትር መቀየር) ፤እና እነዚህን ልወጣዎች ባለብዙ-ደረጃ/multi-step እውነተኛ ፕሮብሌሞችን ለመፍታት ተጠቀም(ሚ)።

### በአስር ቤት ውስጥ ቁጥሮችና ግብረቶች/ስሌቶች

- ባለ-ብዙ-አሃዝ ሙሉ ቁጥሮች በመደበኛ የሂሳብ አሰራር/algorithm በቅልጥፍና ማባዛት።
- በቦታ ዋጋ፣ በግብረቶች ባህርያት፣ እና/ወይም በመደመርና በመቀነስ መካከል ባለው ዝምድና በመገልገል በተጨበጡ ሞዴሎች ወይም ስእሎችና ስልቶች በመገልገል ወደ መቶኛ በማጠጋት ዴሲማሎችን መደመር፣ መቀነስ፣ ማባዛትና፣ ማካፈል፤ ስልቱን ወደ ፅሁፍ ዘዴ ማዛመድ እና ጥቅም ላይ የዋለውን ምክንያታዊነት ማብራራት።

### ግብረቶች እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- ሁለት የተሰጡ ህጎችን በመጠቀም ሁለት የቁጥር ቅጦችን/ተከታታይ ወጥነት ያላቸው ቁጥር ማመንጨት።
- በሁለት ተጓዳኝነት ያላቸው አገላለጾች  መካከል ያለውን ትክክለኛ/ግልጽ ግንኙነት/ተዛማጅነት ለይ።
- ከሁለቱ ቅጦች ተጓዳኝ አገላለጾች የያዙ በቅደም ተከተል የተቀመጡ ጥንዶች መስራት፣ በቅደም ተከተል የተቀመጡ ጥንዶችን በኮኦርድኔት ፕለን ላይ መንደፍ።

### ጂኦሜትሪ

- በእያንዳንዱ መስመር ላይ ከ 0 ጋር ለመገጣጠም የተሰራውን መገናኛ መስመር (መነሻውን) እና በታየዉ ገላጣ/ፐለን ቦታ ለይ የተሰጠ ነጥብ የእነርሱ ኮኦርድኔትስ የሚባሉትን የተደረደሩ ጥንድ ቁጥሮችን በመጠቀም፣ጥንድ ቀጥ ያሉ የቁጥር መስመሮች፣አክስስ የሚባሉ በመጠቀም የተገናኘ/የተቀናጀ ሥርዓት መተርጎም።
  - የመጀመሪያዉ ቁጥር አንዱ ዘንግ በተዘረጋበት አቅጣጫ ከመነሻ ነጥብ ምን ያክል እንደሚርቅ አመላካች መሆኑን ተገንዘብ/ቢ።
  - ሁለተኛው ቁጥር የሚያመለክተው ወደ ሁለተኛው አክሲስ አቅጣጫ ምን ያክል ርቀት እንደሚጓዝ አመላካችና የሁለቱ አክሲሶች ስያሜ እና ኮኦርድኔቶች ጣምራ እንደሚሆኑ መረዳት።
- ተጨባጩን - ዓለም እና የሂሳብ ፕሮብሌምን በመጀመሪያው ዝርግ ቦታ የክብ ሩብ/quadrant የግራፍ ነጥቦች ምልክቶችን በማድረግ በሁኔታዉ ዐውድ ዉስጥ  ነጥቦቹ ያረፉበትን የዋጋ/እሴት ተርጉም(ሚ)።
- በአንድ ምድብ/ፈርጅ ላይ ባለሁለት ማዕዘን እይታ ያላቸው አኃዞች/ቅርፆች ባሕሪይ ለሁሉም ንዑስ ፈርጆች/ምድቦች የመሆን ባሕሪይ እንዳላቸው ተረዳ/ጂ።
  - ለምሳሌ፦ ትይዩ ጎኖቹ እኩል የሆኑ ማዕዘናዊ አራት ጎን ምስሎች (rectangles) አራት ባለ 90 ዲግሪ ማዕዘኖች (right angles) እና ጎኖቹ እኩል የሆኑ አራት ማዕዘን (squares) ማዕዘናዊ አራት ጎን ናቸው፣ በመሆኑም ጎኖቹ እኩል የሆኑ አራት ማዕዘን ሁሉም አራት ባለ 90 ዲግሪ ማዕዘን አላቸው።.
- ባለሁለት ማዕዘን ዕይታ ያላቸውን ምስሎች እንደባህሪያቸዉ ተዋረድ በደረጃ መለየት።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፦ ስነ ፅሁፍ

- ፅሁፉ በግልፅ የሚለውን ሲያብራሩ እና ከፅሁፉ መረጃ ሲወስዱ ከፅሁፉ በትክክል መጥቀስ።
- በጽሑፉ ላይ ካሉት ዝርዝሮች፣ በድራማ ወይም ጭውውት ዉስጥ ያሉ ገጸባህርያት እንዴት ለችግሮች/ቻለንጆች ምላሽ እንደሰጡ ወይም በግጥም ውስጥ ተናጋሪው/ዋ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንዴት እንደሚ(ምታ)ያንጸባርቅ በማካተት፤  የድራማውን ጭብጥ/ፍሬ ሃሳብ መወሰን፤ ጽሑፉን አሳጥር(ሪ)፡
- ከምንባብ/ከጽሑፉ ዉስጥ በልዩ ዝርዝሮች ላይ በማተኮር፣ ከድርሰት/ትረካ፣ ከድራማ፣ ወይም ከግጥም ዉስጥ፣ ሁለት ወይም የበለጠ ገፀ-ባሕሪያትን አወዳድር(ሪ) እና አነፃጽር(ሪ)።
- ተከታታይ ምዕራፎች፣ ትዕይንቶች፣ ወይም ስንኞች በአንድነት ተስማምተዉ/ተቀናጅተዉ የአንድ የተለየ ድራማ አጠቃላይ መዋቅር እንዴት እንደሚያቀርቡ ግለጽ/ግለጪ።
- የተራኪ ወይም የተናጋሪ አስተያየት በክውነቶች አገላለፅ ላይ እንዴት ተፅእኖ እንደሚያደርግ መግለፅ።
- የሚታዩ እና ባለበርካታ-ሚድያ ንጥረነገሮች ለአንድ ፅሁፍ ትርጉም፣ ቃና፣ ወይም ውበት እንዴት እንደሚያበረክቱ መተንተን።
- በ5ኛ ክፍል ደረጃ በሚገባ ውስብስብ የሆነ ስነ-ጽሑፍን አንብቦ መገንዘብ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፦ መረጃዊ

- ከአንድ ፅሁፍ በትክክል መጥቀስ ፅሁፉ በትክክል ምን እንደሚል ሲገልፁ እና ከፅሁፉ ጥቅሶች ሲያወጡ።
- የአንድን ፅሁፍ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዋነኛ አስተሳሰቦች መወሰን እና በቁልፍ ዝርዝሮች እንዴት እንደሚደገፉ ማብራራት፤ ፅሁፉን ማጠቃለል።
- በሁለት ወይም የበለጠ ግለሰቦች፣ ሁኔታዎች፣ ሃሳቦች፣ ወይም ጽንሰሃሳቦች በታሪካዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ወይም ቴክኒካዊ፣ በጽሑፍ ዉስጥ ባለው የተለየ ኢንፎርሜሽን/መረጃ መሠረት ግንኙነታቸውን ወይም ተግባቦት አስረዳ።
- ከ5ኛ ክፍል ርእስ ወይም ርእስ ጉዳይ ጋር በተዛመደ ጽሑፍ ዉስጥ አጠቃላይ የቀለም ትምህርት እና ጎራ ተኮር ቃላት እና ሀረጎች ትርጉም ይወስኑ።
- ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ጽሑፍ ላይ  አጠቃላይ የድርጊቱን ቅንብር፣ ሃሳቦችን፣ ፅንሰሃሳቡቹን፣ ወይም መረጃ/ኢንፎርሜሽን  አወዳደር/ሪ እና አነፃጽር/ሪ።
- በሚወክሉት አስተያየት ውስጥ አስፈላጊ ተመሳሳይነቶችንና ልዩነቶችን እያመላከቱ፣የተመሳሳይ ክውነት ወይም ርእስ በርካታ ትረካዎችን መተንተን።
- አንድ ደራሲ በፅሁፍ ውስጥ የተለዩ ነጥቦችን ለመደገፍ ምክንያቶችንና ማስረጃ እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚያ(ምታ)ውል ማብራራት፣ የትኛው ምክንያትና ማስረጃ የትኛውን ነጥብ/ቦች እንደሚደግፍ በመለየት።
- በአርእስቱ ላይ በእዉቀት መፃፍ ወይም መናገር እንዲቻል ከተለያዩ ፅሁፎች በተመሳሳይ ርእስ መረጃ ማዋሐድ።
- ለ5ኛ ክፍል በአግባቡ ውስብስብ የሆኑ መረጃያዊ ፅሁፎችን ማንበብ እና መገንዘብ።

### ቋንቋ፦ የቃላት ዝርዝር ግኘት እና አጠቃቀም

- ስለ 5ኛ ክፍል ርእሶችና ፅሁፎች፣ በሌሎች አስተሳሰቦች ላይ እየገነቡ እና የየራሳቸውን በግልፅ እየገለፁ በተለያዩ በትብብሮሽ ውይይቶች ላይ በውጤታማነት መሳተፍ።
- ድምፅ ከፍ ተደርጎ የተነበበ ፅሁፍን ወይም በተለያዩ ሚድያና፣ በሚታይ፣

የብዛት እና የቃልን የሚያካትቱ ቅርፀቶች የቀረበ መረጃን ማጠቃለል።

- የአንድን ተናጋሪ ንግግር ፍሬነገሮችን በማጠቃለል እና የተባሉትን ነገሮች በምክንያት እና በመረጃ የተደገፉ መሆናቸውን አስረዳ(ጂ)።
- ያልታወቁ እና በርካታ ትርጉም ያላቸውን ቃላት እና ሃረጎች በ5ኛ ክፍል ምንባብ ይዘት የተመሰረቱ፣ ከተደረደሩት ስልቶች እየለዋወጡ በመምረጥ፣ ትርጉማቸውን መወሰን ወይም መግለጽ።
- የዘይቤያዊ አነጋገር፣ የቃል ዝምድና፣ እና በቃል ትርጉሞች ውስጥ የሽሙጦችን ግንዛቤ ማሳየት።
- ለክፍል ደረጃ የሚመጥን ትክክለኛና አጠቃላይ የአካደሚክ እና የተለየ-ጎራ/domain-specific ቃላት እና ሃረጎችን፣ የማነፃጸሪያ ምልክቶችን፣ የመጨመር እና ሌሎች ተያያዥ/ሎጂካል ግንኙነቶችን ጠቋሚ የሆኑትን ጨምሮ ማግኘት እና መጠቀም።

## ስነ-ጽሑፍ

### ትምህርት ሰጭ/ገላጭ

- አንድን ርእስ ለማገናዘብና እስተያየቶችንና መረጃዎችን በግልፅ ለማስተላለፍ መረጅያዊ/ገላጭ ፅሁፎች መፃፍ።
- ጠቅለል ባለ ምልከታ እና ትኩረት ፤ እና ከቡድን ጋር የሚገናኝ አግባብነት ያለው(ሎጂካል) መረጃ/ኢንፎርሜሽን፣ የጽሑፍ አቀራረብ/አቀማመጥ/formatting (ለምሳሌ፡- ዋና ርእሶችን)፣ ስዕላዊ መግለጫ/አገላለጽ፣ እና እውቀት ለማግኘት አስፈላጊ ሲሆን ብዝሃ ሚዲያ በመጨመር አንድን አርእስት በትክክል አስተዋውቅ/ቂ።
- በመረጃዎች፣ ፍቺ፣ ተጨባጭ ዝርዝሮች፣ ጥቅሶች፣ ወይም ሌላ ከርእሱ ጋር በሚገናኙ መረጃዎች/ኢንፎርሜሽን እና ምሳሌዎች ርእሱን አዳብር(ሪ)።
- በቀረበው ሀሳብ/ማብራሪያ ላይ የማጠቃለያ መግለጫ ወይም ክፍል ስጥ/ጪ።

### ትረካ

- እውነተኛ ወይም ሃሳብ የወለዳቸው ተሞክሮዎችን ወይም ክውነቶችን ለማዳበር ውጤታማ ቴክኒክ፣ ገላጭ ዝርዝሮች፣ እና በጠሩ የክነት ቅደም-ተከተሎች በመጠቀም ትረካዎችን መጻፍ።
- ሁኔታን በማመቻቸት እና ተራኪ እና/ወይም ገፀባህርያት በማስተዋወቅ አንባቢው(ዋ)ን ማስተናገድ/ማላመድ፤ ተፈጥሯዊ በሆነ ሁኔታ የሚከሰት የክውነት ቅደም-ተከተል ማደራጀት።
- ተሞክሮዎችንና ክውነቶችን ለማዳበር ወይም የገፀባህርያትን ምላሾች ለሁኔታዎች ለማሳየት፣ ውይይት፣ ገለፃ፣ እና እርምጃ በመሳሰሉ የትረካ ቴክንኮች መጠቀም።
- የተለያዩ የክስተቶችን/የክውነቶችን ቅደም ተከተሎች ለመቆጣጠር በተለያዩ የሽግግር ቃላት፣ ሃረጎች እና አንቀፆች መገልገል።
- ሁነቶችን እና ልምዶችን በዝርዝር ለማስተላለፍ ተጨባጭ ቃላቶችን እና አረፍተነገሮችን እና ስሜታዊ ዝርዝሮችን ተጠቀም(ሚ)።
- ከተተረኩ ተሞክሮዎች ወይም ክውነቶች የሚከተል አንድ መደምደሚያ ማቅረብ።

#### አስተያየት

- በርእሶች ወይም በፅሁፎች ላይ በምክንያቶችና በመረጃዎች እየደገፉ የአመለካከት አጫጭር ድርሰቶችን አስተያየት ፃፍ/ፊ።
- አንድ ርእስ ወይም ፅሁፍን በጥራት ማስተዋወቅ፣ እስተያየት ማስቀመጥ፣ እና አስተያየቶች በሃቆችና በዝርዝሮች የተደገፉበት፣ እና የፀሃፊው(ዋ)ን አላማ ለመደገፍ በሎጂክ የተመደቡበት ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር።
- በቃላቶች፣ ሃረጎች፣ እና በአንቀፆች (ለምሳሌ፣ በተከታይ፣ በተለይ) በመጠቀም አስተሳሰብንና ምክንያቶችን ማገናኘት።
- ከቀረበው ሃሳብ ጋር የሚገናኝ ማጠቃለያ/የመደምደሚያ ሃሳብ መግለጫ ስጥ/ጪ።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- እድገቱና አደረጃጀቱ ለተግባር፣ አላማ፣ እና ለአድማጭ ተገቢ የሆነ ጥራት ያለውና ስሙሙ ፅሁፍ ማቅረብ።
- ከእኩዮችና ከአውቂዎች አመራርና ድጋፍ ጋር፣ ፕላን፣ ክለሳ፣ አርትኦ፣ ዳግመ-ፅሁፍ፣ ወይም አዳዲስ ሙከራ እንደአስፈላጊነቱ በማድረግ፣ ፅሁፍን ማዳበርና ማጠናከር።
- በአንድ ረእሰ ጉዳይ ዙሪያ የተለያዩ ነገሮችን በመመርመር እውቀትን ለመገንባት በርካታ ምንጮችን የሚጠቀሙ የአጭር ምርምር ፕሮጀክቶችን ማካሄድ።
- ትንተና፣ ሃሳብ፣ እና ምርምር ለመደገፍ ከስነፅሁፋዊ ወይም መረጃያዊ ፅሁፎች ማስረጃ መውሰድ።
- ለተለያዩ ሥርዓት-ተኮር ተግባራት፣ አላማዎች እና ታዳሚዎች ዳጋግሞ ለረጅም የጊዜ መቃኖች (የምርምር፣ ማሰላሰያ፣ እና የክለሳ ጊዜ) እና አጠር ላሉ የጊዜ መቃኖች (ለአንድ-አፍታ ወይም ለአንድ ወይም ሁለት ቀን) መፃፍ።

### የቋንቋ አጠቃቀም

- ዋነኛ አስተሳሰቦችን ወይም ዘውጎችን ለመደገፍ በአንድ ርእስ ወይም ፅሁፍ ዘገባ ማቅረብ ወይም አስተሳሰቦችን በሎጂክ ቅደም-ተከተል በመስጠት እና በተገቢ ሃቆችና አስፈላጊ፣ ገላጭ ዝርዝሮች በመጠቀም፣ አንድ ሃሳብ ማቅረብ፤ ሊገባ በሚችል ፍጥነት በግልጽ ይናገሩ።
- የዋነኛ አስተሳሰቦች ወይም ዘውጎች እድገትን ለማበልፀግና መግለጫ ሲሰጥ ተገቢ ሲሆን ባለ-በርካታ-ሚድያ (ለምሳሌ፣ ግራፊኮች፣ ድምፅ) እና የሚታዩ ትርእይቶች ያካቱ።
- ንግግርን ከተለያዩ አውደንባቦችና ትግባሬዎች ጋር ማስማማት፣ ለተግባርና ለሁኔታ ተገቢ ሲሆን በመደበኛ እንግሊዘኛ በመጠቀም።
- በመፃፍና በንግግር የመደበኛ እንግሊዘኛ ስዋስውና አጠቃቀም ደንቦች በቂ ችሎታ ማሳየት።
- በፅሁፍ የመደበኛ እንግሊዝኛ በትልቅ ፊደል አጠቃቀም/capitalization፣ በስርአተ ነጥብ እና በስፔሊንግ ደንቦች በቂ ችሎታ ማሳየት።
- ለትርጉም፣ ለአንባቢ/አድማጭ ፍላጎት፣ እና ለዘየ አረፍተነገሮችን ማስፋፋት፣ መገጣጠም፣ እና መቀነስ።
- በትረካ/ታሪኮች፣ በድራማዎች፣ ወይም በስነግጥሞች ላይ የሚጠቀሙትን የእንግሊዝኛን የተለያየ ገጽታ (ለምሳሌ፡- የአነጋገር ዘዬ፣ ስሜትን አገላለጽ/የቋንቋ አጠቃቀም ደረጃ) ማወዳደር እና ማነፃጸር።

## ሳይንስ

### የህይወት ሳይንሶች

- እጽዋት እና እንስሳት ከምንጭ/ዘር የሚወርሱት መለያ ባህርይ እንዳላቸው መረጃ ለመስጠት እና እነዚህ ባህሪያት ተመሣሣይነት ባላቸው ፍጡራን ላይ እንደሚኖር ትንታኔ እና ትርጉም በመስጠት ጭብጥ መረጃ አቅርብ/ቢ።
- የአካባቢ ሁኔታ በባህርይ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል የሚለዉን ማብራሪያ ለመደገፍ ማስረጃዎችን ይጠቀሙ።
- እንስሣት በስሜት ህዋሳቶቻቸው አማካይነት የተለያየ ኢንፎርሜሽን እንደሚያገኙ፣ በአእምሯቸው ኢንፎርሜሽኑን እንደሚያዋህዱ፣ እና ለኢንፎርሜሽኑ በተለያየ መንገድ ምላሽ እንደሚሰጡ አንድ ሞዴል/ምስል/ቅርጽ በመጠቀም አስረዳ(ጂ)
- እጽዋት እና እንስሳት ለመኖር/ህልውና፣ ለእድገት፣ ለባህሪ፣ እና ለመባዛት የሚረዳቸው ውስጣዊ እና ውጫዊ መዋቅር/አሠራር እንዳላቸው የውይይት/የመከራከሪያ ሃሳብ አዘጋጅ(ጂ)።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ስነ-ነዋይ/ኤኮኖሚክስ

- የቴክኖሎጂ ለውጦች በሜሪላንድ ውስጥ በምርት እና ፍጆታ/ተጠቃሚነት ላይ እንዴት ለውጥ እንዳመጣ አስረዳ/ጂ።
- የሜሪላንድን ክልላዊ የሙአለንዋይ/ኤኮኖሚ ልዩ ሁኔታ እና ሰዎች እንዴት እንደሚኖሩና የሚሰሩበትን መንገዶች ግለጽ(ጪ)።
- በሜሪላንድ ያለውን የኤኮኖሚ ስርአቶችን አስረዳ(ጂ)።

### *የገንዘብ ትምህርት*

- ሰዎች ስለገንዘብ/ፋይናንሳዊ ምርጫ የሚያደርጉት በሃብት ውስንነት፣ በአስፈላጊነት/በሚያስፈልጋቸው፣ እና በሚወዱት/በሚፈልጉት ነገር መሆኑን ግለጽ(ጪ)።
- ሁኔታን/ጸባይ/አመለካከት፣ አስተሳሰብ እና የባህሪ መገለጫዎች ስለ ገንዘብ፣ ስለቁጠባ፣ ስለ ኢንቨስት ማድረግ፣ እና ስለ ሥራ እንዴት በግል ሸማቹ ውሳኔዎች ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ ግለጽ/ጪ።
- የተለያዩ የገቢያ ዓይነቶችን ግለጽ/ግለጪ።
- በትምህርት፣ ክህሎት፣ የሙያ ምርጫ፣ የኤኮኖሚ ሁኔታዎች፣ እና በገቢ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች አወዳድር/ሪ።
- የክሬዲት ምርቶች ከአገልግሎቶች ልዩነቱን አሳይ።
- የሽያጭ ዘዴ/ቴክኒክን ጨምሮ የቢዝነስ ሥራዎችን ውጤታቸውን መርምር(ሪ)።

## *መረጃያዊ/የኢንፎርሜሽን መሠረተ ትምህርት*

- የመረጃ ፍላጎትን ለማሟላት የተዘገቡ አሃኦች/መረጃዎች ጥራት መገምገምና መተንተን።
- የአንድን መረጃ ፍላጎት ለማሟላት ጥያቄዎችን ማስቀመጥና ማጣራት።
- ከቃለ መጠይቆች እና/ወይም ከዳሰሳዎች አዲስ መረጃ/ኢንፎርሜሽን

ፍጠር(ሪ)።

- አሃዞችን/መረጃዎችን በተለያዩ ቅርፀቶች መመዝገብ፡፡
- የተፈላጊ መረጃን ግኝቶች/መደምደሚያዎች ለማጋራት ለማዘጋጀት በተለያዩ ቅርፀቶች መጠቀም።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።
- ሪኮርድ ከተደረገ መረጃ/ዳታ/ኢንፎርሜሽን ላይ፣ ከተፈለገው መረጃ ጋር የሚገናኙ አዳዲስ እውቀትና ግንዛቤዎችን በስነምግባር ፍጠር/ሪ

## ስነጥበብ

### የሥነ ጥበብ ፈጠራ እና ከሥነ ጥበብ ጋር መገናኘት

- ለስነጥበብ ሥራ የፈጠራ መፍትሔዎችን ለማፍለቅ ሃሳቦችን አጠናቅር(ሪ)።
- ሃሳብን፣ ስርአተ ሒደት፣ ወይም ውጤት ለማስተላለፍ፣ የስነጥበብ መሠረታዊ ንጥረነገሮችን እና የንድፍ መርሆችን ተጠቀም(ሚ)።
- የእደጥበብ መሥሪያዎችን፣ ሚዲያ፣ እና የሥራ ቦታን ሲጠቀሙ ተገቢውን የሥነጥበብ መሥሪያ ዘዴዎችን/ቴክኒኮችን እና ሥርአቶችን ይምረጡ።
- የእደጥበብ ሥራን ትርጉም ለማዳበር እና የእጅ ሙያን ለማሻሻል ግብረመልስ/ምላሽ አስተያየትን ተግባራዊ አድርግ(ጊ)።
- ለለውጥ ምላሽ  የኪነጥበብ ስራ ይፍጠሩ።
- እምነትን፣ እሴትን፣ ወይም ባህርይን ለመለወጥ ስነጥበብ እንዴት እንደሚጠቅም አስረዳ(ጂ)።

### የኪነጥበብ አቀራረብ እና የኪነጥበብ ግብረመልስ

- የሥነጥበብ ሥራን በመምረጥ በአርቲስቱ/ቷ አገላለጽ መሠረት እንዴት የአውደርዕይ መስፈርት እንደሚያሟላ ግለጽ(ጪ)።
- የእደጥበብ ሥራን በተለየ የአውደርዕይ/የኤግዚቢሽን ስፍራ/ቦታ ለማቅረብ አመቺ/ተገቢ ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርግ(ጊ)።
- ከጊዜ ወደ ጊዜ የእደጥበብ ሥራ እንዴት እየተለወጠ እንደሄደ የሚያሳዩ በግል የተሰበሰቡ የስነጥበብ ውጤቶችን አስረዳ(ጂ)።
- አጽንኦት/ትኩረት የስነጥበብ ሥራህ(ሽ)ን ግምገማ እንዴት እንደሚለውጥ አስረዳ(ጂ)።
- የስነጥበብ ስራን በዝርዝር መገምገም የመነሻ ትርጉሙን እንዴት እንደሚለውጥ አስረዳ(ጂ)።
- በግል የታቀደ የስነጥበብ ሥራ ግቡን መትቶ እንደሆነ ለማረጋገጥ መስፈርት መርጠህ(ሽ) ተጠቀም(ሚ)።

## ሙዚቃ

### የሙዚቃ ዝንባሌ/ምላሽ መስጠት

- እያዳመጥክ(ሽ)፣ እየተወዛወዝክ(ሽ) በአገላለጽ/አቀራረብ ጥራቶች ላይ ያለውን ለውጥ ለይ።

### ሙዚቃ መጫወት

- ከፍ ባለ የድምፅ አገላለጽ እና በግልጽ ቃላት ዘምር(ሪ)።
- በህብረት የሚዘመሩ መዝሙሮችን እና ሐረግ ያለዉ ዝማሬ በትክክል ዘምር(ሪ)።
- ከተለያዩ ባህሎች የሙዚቃ መሣሪያዎችን አጨዋወት በትክክለኛ የአጨዋወት ቴክኒክ/ስልት አሳይ።
- በቡድኖች ውስጥ ሆኖ መዘመር፣ ተምቡሮችን በመደባለቅ እና ዳይናሚክ ደረጃዎችን በማጋጠም።
- ባህላዊ ዘፈን እና ባህላዊ ጭፈራዎችን ከተለያዩ የአለም ባህሎች ማቅረብ።

**የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት**

- እንድ ቀላል ዜማ በትሬብል ስታፍ በተለያዩ ቁልፎች በሶልፌጅዮ ወይም በተመጣጣኝ ስርኣት ማንበብና መጫወት።
- መደበኛ የሙዚቃ ምልክት/ኖታ በመጠቀም አራት- ልከጊዜ ጣዕመዜማዎችን በትሬብል ስታፍ ላይ ወዲያዉ/ያለ ዝግጅት ጻፍ(ፊ)።

**የሙዚቃ ፈጠራ**

- ልዩ ልዩ የድምፅ ምንጮችን፣ የተለመዱ/የታወቁ ድምፆችን፣ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ያልተለመዱ ድምፆችን፣ እና በሰዉነት ምት ጭምር በመጠቀም እዚያው በዚያው አጫጭር የሙዚቃ መሣሪያ ዜማዎችን ፍጠር(ሪ)።
- የተለያዩ የድምፅ ቃናዎችን፣ የባህላዊ ዜማ ድምጾችን እና ሌሎችንም ባህላዊ ያልሆኑ የዜማ ድምጾችን ጭምር በመጠቀም እዚያው በዚያው ፍጠር(ሪ)።
- የመሰረቱን/ኦሪጅናል ድምጽ እና ስንኝ በመጠቀም አጫጭር የሙዚቃ ቃና ድርሰት በሙዚቃ ኖታ ጻፍ/ፊ።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

**ጤንነትን የሚያበለጽግ- ኣካላዊ ብቃትና እንቅስቃሴ**

- የሰውነት እንቅስቃሴ በአካላዊ ሥርዓት/ሲስተም ላይ የሚኖረውን ውጤት በመተንተን አሳይ።
- የሰውነት አቋም ደረጃን ለማስተካከል  አስፈላጊ ነገሮችን (ዝውተራ፣ መግነን/በጥብቅ/Intensity፣ ጊዜ፣ ዓይነት) የ FITT ን መርህ ተለማመድ/ጂ።
- የ FITT መርህ በመከተል የአካል አቋም ብቃት እቅድ ንደፍ(ፊ)።

**የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች**

- አጭር እጀታ እና ረዥም እጀታ ባላቸው መሣሪያዎች ምትን አሳይ።

## የጤና ትምህርት

**የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ (DCP)**

- በተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች መካከል ያለዉን ልዩነት መለየት።
- ሰውነት በሽታን/ቁስለትን እንዴት እንደሚፋለም አስረዳ(ጂ)።
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን (HIV/AIDS) እንደ አንድ ተላላፊ በሽታ ግለጽ/ጪ።
- በበሽታዎች የመያዝ ስጋትን የሚጨምሩ የግል የዕለት ተእለት የኑሮ ልማዶችን እና ምርጫዎችን ይተንትኑ።